ነሐሴ ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፱ (ሴቭቴምበር 1/2007)

# እንኳን አደረሳችሁ አሲምባዎች!

(ከአያልነሽ)

ሠላምታዬ ይቅደም እንደምን አላችሁ
በቀናት መቁጠሪያ ወራት አስልታችሁ፣
ነሐሴ 26 ደረሰ ብላችሁ፣
ለዝክረ ሰማዕታት ግብዣ ካረጋችሁ፣
አሲምባ! አሲምባዎች እግዚአብሔር ይስጣችሁ።

ነሐሴ ሃያ ስድስት በስድሳ ሰባት፣
ለጋ ለጋ ልጆች ለግላጋ ወጣት፣
በሐገር ፍቅር ነደው፣ ለሀገር ለመሞት፣
ተሽቀዳድሞን መሞት አድርገው ኩራት፣
ስንት ጀግና አየነ፣ ስንት ሰማዕታት።

ይናገር ይመስክር፣ የኢትዮጵያ መሬት፣
ከተማው አፍ ያውጣ፣
ቀብሮ ጀግንነትን ለውርደት ከሚያሳጣ፣
ይቆፈር አፈሩ፣ ደም የጎረፈበት፣
አጥንቱ ይመርመር ምልክት አለበት፣
ውርደትን አዋርደው፣ ታሪክ የፃፉበት፣
ኢሕአፓ ያቸንፋል ብለው ያለፉበት፣
ይዘከር ታሪኩ በእውነት እንደበት።

ይናገር ገጠሩ፣ የኢትዮጵያ መሬት፣
አጥንት ተከስክሶ ደም የፈሰሰበት፣
ሥጋ ተቆራርጦ በአውሬ የተበላበት፣
ከፋሽስቶች ጋራ የተጋደሉበት፣
ከጠባቦች ጋራ የተዋደቁበት፣
ኢትዮጵያን ወደው ነው ምስጢርም የለበት።

ይነገር ካላችሁ ታሪኩ ይነገር፣
ይዘከር ካላችሁ ታሪኩ ይዘርዘር፣
ይፃፍም ካላችሁ ቀለሙም አይነጥፍ፣
በእያንዳንዱ ገላ ተሰርቷል ስንት ግፍ።

ምነው አይናገር ታሪክ አፍ አውጥቶ፣
የሰው አውሬነቱ በአደባባይ ታይቶ፡
በጠራራ ፀሐይ፣ ሬሳ ተሰጥቶ፣
ወላጅ በቁመናው፣ ሁለት ሞት ሞቶ፣
የልጁን ሬሳ በገንዘቡ ገዝቶ።

ይሄ ሆኖ እያለ ጭካኔው ሲፈታ
በቁመና እያለን፣ ታሪክ ከተምታታ
ሐሰት አፍ አውጥቶ ካሰማ ስሞታ፣
ሙግት እንገጥማለን እውነት እስኪረታ።

ስለዚህ! አሲምባዎች
እንደን ሰማእታቶች፣ የዚያን ትውልድ ፈርጦች፣
የዘመኑ አበባ፣ የዘመኑ እምቡጦች፣
ይነገር ገድላቸው ይፃፍ በሚገባ፣
ታሪኩ ይዘርዘር፣ መስከረም ሳይጠባ፣
ለምስክርነት! ይኸው ተጋብዘናል እኛም ወደ አሲምባ።

ሰማዕታቶቻችን የትግላችን ተስፋ ናቸው!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!